# ለጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ ለሚሉ ሕጻናት የጨቅላነት ጊዜ ድጋፍ



Washington State Department of Early Learning

## 14.C የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ መመሪያዎች

### 14.C.1. መግቢያ

(a) የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ሕግ (IDEA) ክፍል ሐ የተሟላ፣ የተቀናጀ እና የተለያዩ ኤጀንሲዎችን የሚያስተሳስር አካል ጉዳት ላለባቸው ጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማቀናጀት በኮንግረሱ የተረቀቀ ሕግ ነው። ኮንግረሱ ይህንን የህዝብ ክፍል የሚያገለግሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች አስቀድመው የነበሩ ለመሆናቸው ዕውቅና በመስጠት እነዚህን ፕሮግራሞች ለማስተባበር የሚረዱ መሰረተ ልማቶችን ለማቅረብ ክፍል ሐን ነድፏል። በዚህም መሰረት፣ ለክፍል ሐ የገንዘብ ምንጭ የፌዴራል፣ የግዛት፣ እና የአካባቢ የገንዘብ ምንጮችን የመንግስት እና የግል ኢንሹራንስን ጨምሮ እንዲጠቀሙ ተነድፏል። ሁሉንም የድጋፍ አገልግሎቶ ወጪዎች ለመሸፈን የሚበቃ፣ በቂ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ባለመኖሩ፣ ሁሉም የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች በመንግስት ወጪ ሊሰጡ አይችሉም። ቤተሰቦች ልጆቻቸው ለሚያገኟቸው ፕሮግራሞች በገንዘብ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይጠበቃል። ይህ ግዴታ፣ የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ለሚፈለግባቸው የESIT የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች የግል የጤና እንክብካቤ/የመድን ዋስትናን እና አፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን ለመጠቀም በመፍቀድ ሊሟላ ይችላል።

(b) በርካታ ቁጥር ያላቸውን ጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት እና ቤተሰቦቻቸውን ለማስተናገድ ሲባል እያንዳንዱ ግዛት የእነዚህን ሐብቶች አጠቃቀም የማሳደግ ኃላፊነት ተጥሎበታል። በተጨማሪም እነዚህ የገንዘብ ምንጮች ለልጁ ዕድገት ጥቅም የሚሰጡ አጥጋቢ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት መዋላቸውን ማረጋገጥ በ ESIT ላይ የተጣለ ኃላፊነት ነው። ESIT ሰፋ ያለ የብቁነት መስፈርቱን ይዞ እንዲቆይ፣ የመንግስት የመድን ዋስትናን የግል የመድን ዋስትናን እና ክፍያዎችን ጨምሮ ሊገኙ የሚችሉ የገንዘብ ምንጮችን በሙሉ መጠቀሙ ወሳኝ ነው።

### 14.C.2. አጠቃላይ መመሪያዎች

(a) በ34 CFR §303.521(e)(2)(i) መሰረት የ ESIT አገልግሎት ሰጪዎች የሚከተሉትን ከወላጆች በሚጠይቁበት ጊዜ የክፍያ ሥርዓትን እና የክፍያዎች ፖሊሲን የጽሁፍ ቅጂ ይሰጣሉ፡-

(1) በግል በሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ስብሰባ ላይ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት ፈቃድ በሚቀበሉበት ጊዜ፤ እና

(2) ለክፍል ሐ አገልግሎቶች ለመክፈል የመንግስት ወይም የግል የመድን ዋስትናን በሚጠቀሙበት ጊዜ።

(b) ወላጆች የ ESIT የክፍያ ሥርዓት እና የክፍያዎች ፖሊሲ እንዲደርሳቸው ተደርጎ የወላጆች ፈቃድ ካልተገኘ በስተቀር ከመንግስት ወይም ከግል የመድን ዋስትና ክፍያ መጠየቅ ሊከናወን አይችልም።

(c) የሚከተሉት ተግባራት እና አገልግሎቶች በመንግስት ወጪ በ ESIT መሰጠት ያለባቸው ሲሆን ቤተሰቦች ለእነዚህ ማንኛውንም ዓይነት ወጪ አያወጡም፡-

(1) ከ34 CFR §§303.301 እስከ 303.303 ያለውን ልጅን ፈልጎ የማግኘት መስፈርቶች መተግበር።

(2) በ 34 CFR §§303.320 መሰረት ግምገማ እና ምዘና እንዲሁም በ34 CFR §§303.13(b) መሰረት ከግምገማ እና ምዘና ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች።

(3) አገልግሎት የማስተባበር አገልግሎቶች (የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ)፣በ 34 CFR §§303.13(b)(11) እና

303.33 በተሰጠው ትርጓሜ መሰረት።

(4) አስተዳደራዊ እና የማስተባበር ኃላፊነቶች

(i) ከ 34 CFR §§303.342 እስከ 303.345 ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት በ IFSPs እና በጊዜያዊ IFSPs ዝግጅት፣ ክለሳ፣ እና ግምገማ፤ እና

(ii) ከ 34 CFR §§303.400 እስከ 303.511 ያሉትን የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎች እና ሌሎች ከ 34 CFR §§303.300 እስከ 303.346 ያሉ ግዛት አቀፍ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ስርዓቶችን ሌሎች ይዘቶችን መተግበር።

(d) ከመንግስት የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና እና/ወይም ከግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና የገንዘብ ክፍያ ከመጠየቁ በፊት ቤተሰቦች የገቢ እና ወጪ መረጃ፣ ማንነትን ለመግለጽ የሚያስችሉ መረጃዎችን እና የመንግስት እና/ወይም የግል የመድን ዋስትና ሽፋንን ለማገናኘት ፈቃድ መስጠት አለባቸው። የገቢ እና ወጪ መረጃ የሚያገለግለውየቤተሰቡን የመክፈል ችሎታ ወይም መክፈል አለመቻል ለመወሰን ነው። የቤተሰብ የመክፈል ችሎታ ወይም መክፈል አለመቻል አቋም ቢያንስ በየአመቱ እና ቤተሰብ ሲጠይቅ ደግሞ ከዚያ ባነሰ ጊዜ ይገመገማል እንዲሁም ይሻሻላል።

(e) በ34 CFR §303.521(a)(4)(ii) መሰረት “መክፈል አለመቻል” የሚለውን ትርጓሜ የሚያሟሉ እና ቤተሰቦች በክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች መሰረት በልጃቸው IFSP ላይ የተመለከቱትን ሁሉንም የክፍል ሐ አገልግሎቶች ያለምንም ወጪ ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም የቤተሰቡ መክፈል አለመቻል የክፍል ሐ አገልግሎቶች እንዲዘገዩ ወይም እንዲከለከሉ አያደርግም።

(f) በ34 CFR §303.520(a)(2)(i) እና (iii) መሰረት፣ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች የክፍል ሐ አገልግሎቶችን ለመስጠት እንደ ቅድመ ሁኔታ የአንድን ወላጅ በመንግስት ጥቅማ ጥቅም ወይም የመድን ዋስትና ፕሮግራሞች መመዝገብ ሊያስቀምጡ አይችሉም እንዲሁም ልጁ ወይም ወላጆቹ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ካልተመዘገቡ የልጁን ወይም የወላጁን የመንግስት ጥቅማጥቅሞች ከመጠቀም በፊት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ወላጅ በአፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ውስጥ መመዝገብ ካልፈለገ ወይም እንዲጠቀሙት ፈቃድ ካልሰጠ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች ቤተሰቡ ፈቃድ የሰጠባቸው የ IFSP አገልግሎቶችን የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች መስጠት አለባቸው። በዚህ ክፍል መሰረት ለልጁ ሊሰጡ የሚገቡ አገልግሎቶች አፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን ለመጠቀም ፈቃድ ስላልተሰጠ ብቻ ሊዘገዩ ወይም ሊከለከሉ አይገባም።

(g) በ 34 CFR §§303.520(a)(3)(iv) እና (b)(1)(ii) መሰረት የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን በመጠቀም ምክንያት ቤተሰቡ ሊያወጣቸው የሚችላቸውን ወጪዎች አጠቃላይ የወጪ መደብ የሚገልጽ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይሰጣሉ፤ እነዚህም የሚከተሉትን የመሳሰሉ ናቸው፡

(1) በልጁ፣ በቤተሰቡ፣ ወይም በልጁ ቤተሰብ አባላት የኢንሹራንስ ፖሊሲ መሰረት በዓመታዊ ወይም የሕይወት ዘመን ሽፋን የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና ጣሪያ ላይ የተከታተቱ ጥቅማ ጥቅሞችን ማጣትን ጨምሮ የትብብር ክፍያዎች፣ የጋር የመድን ዋስትና፣ አሹራዎች፣ ወይም ተቀናሾች እና ሌሎች የረዥም ጊዜ ወጪዎች፤

(2) የቤተሰቡን የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናውን መጠቀም የአካል ጉዳት ላለበት ልጅ፣ ለወላጅ ወይም በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ሽፋን ለተሰጣቸው የልጁ ቤተሰብ አባላት የመድን ዋስትና ሽፋን ለማግኘት አሉታዊ ተጽዕኖ የመፍጠር ዕድል ያለው መሆኑ፤ ለክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች በመክፈሉ የተነሳ የመድን ዋስትና ሽፋን ሊቋረጥ የሚችል መሆኑ፤ ወይም

(3) ለጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ለመክፈል የግል የመድን ዋስትናን መጠቀም የመድን ዋስትናው የአሹራ ክፍያ ላይ ተጽዕኖ ያለው መሆኑ።

(h) በ34 CFR§303.520(a)(2)(ii) መሰረት፣ የአፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን መጠቀም ከሚከተሉት መካከል ማንኛውንም ውጤት የሚያስከትል ከሆነ፣ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች የቤተሰብ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለባቸው፡-

(1) ለልጇ ወይም ለሌሎች የቤተሰቤ አባላት በተሰጠው የሕይወት ዘመን ሽፋን ላይ ወይም በሌሎች የመድን ዋስትና በተሰጠባቸው ጥቅማ ጥቅሞች ላይ መቀነስን የሚያስከትል ከሆነ፤

(2) በሌላ አኳሃን በሜዲኬይድ ሊከፈሉ ይችሉ ለነበሩ አገልግሎቶች ክፍያ መፈጸም ያለባቸው መሆኑን የሚያስከትል ከሆነ፤

(3) በማናቸውም አይነት የአሹራ ክፍያዎች ላይ ጭማሪ የሚያስከትል ወይም የልጁን ወይም የሌሎች

የቤተሰብ አባላትን ሜዲኬይድ ሽፋን የሚያሰረዝ ከሆነ፤ ወይም

(4) በአጠቃላይ ጤና ነክ ወጪዎች መሰረት ለቤት እና ለማህበረሰብ መር የሙብት ሙተው የልጁን ወይም የሌሎች የቤተሰብ አባላትን ብቁነት ለማጣት የሚያሰጋ ከሆነ።

(i) በ34 CFR §303.521(e) መሰረት፣ የ ESIT አገልግሎት ሰጪዎች አፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን ወይም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን መጠቀምን፣ የክፍያዎችን አወሳሰንን እና የግዛቱን የወላጅ የመክፈል ችሎታ ወይም መክፈል አለመቻል አወሳሰንን በተመለከተ ለወላጆች የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎችን የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይሰጣል።

(j) ወላጆች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፡-

(1) በ 34 CFR §303.431 መሰረት በግልግል ሥርዓት ላይ መሳተፍ፤

(2) በ 34 CFR §303.436 ወይም §303.441 የትኛውም አግባብ ይሁን፣ የክስ መስማት ሂደት መጠየቅ፤

(3) በ34 CFR §303.434 መሰረት ለግዛቱ፤ እና/ወይም

(4) ግዛቱ ፋይናንስ ነክ ቅሬታዎችን ለማፋጠን የዘረጋቸው ሌሎች ማናቸውም ሥርዓቶች ቅሬታ ማቅረብ።

(k) በማንኛውም ጊዜ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት ፈቃድ በሚጠየቅበት ጊዜ ወላጆች የክፍያ ሥርዓት እና የክፍያዎች ፖሊሲ እንዲደርሳቸው ሲደረግ ወላጆች ስለ እነዚህ መብቶች እንዲያውቁ ይደረጋል።

## 14.C.3. አፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ወይም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና አጠቃቀም መመሪያዎች

(a) ልጆቻቸው በአፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ውስጥ የተመዘገቡ ቤተሰቦች የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ እንዲደረግባቸው ለሚታዘዙ የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ክፍያ የሚጠየቀው ከአፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ እንደሆነ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። ቤተሰቦችም ክፍያ ለመጠየቅ አገልግሎት ሲባል የልጃቸውን ማንነት ለመግለጽ የሚያስችል መረጃ እንዲሰጥ ፈቃዳቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ ይጠየቃሉ። የተፈረመው ቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ፣የመንግስት እና/ወይም የግል የመድን ዋስትናን ለማገናኘት የተሰጠ ፈቃድ እና የገቢ እና ወጪ ማረጋገጫ ቅጽ ቅጂ ለቤተሰቡ ይሰጣል።

(b) የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና ያላቸው ቤተሰቦች የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ እንዲደረግባቸው ለሚታዘዙ የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ክፍያ ለመጠየቅ ፈቃዳቸውን በጽሁፍ እንዲሰጡ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

(c) በቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ እና በገቢ እና ወጪ ማረጋገጫ ቅጽ ውስጥ የሚገኘው የመንግስት እና ወይም የግል የመድን ዋስትናን ለመጠቀም የሚሰጥ ፈቃድ ቤተሰቡ የቤተሰቡን የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና በመጠቀሙ የተነሳ ሊያወጣቸው የሚችላቸውን ወጪዎች አጠቃላይ የወጪ መደቦች የሚገልጽ የጽሁፍ መግለጫ መያዝ ይኖርበታል።

(d) የተፈረመው ቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ፣የመንግስት እና/ወይም የግል የመድን ዋስትናን ለማገናኘት የተሰጠ ፈቃድ እና የገቢ እና ወጪ ማረጋገጫ ቅጽ ቅጂ ለቤተሰቡ ይሰጣል።

(e) በ IFSP አገልግሎቶች ድግግሞሽ፣ ርዝመት፣ የቆይታ ጊዜ ወይም የጥንካሬ መጠን ላይ ጭማሬ በሚኖርበት ጊዜም የቅድሚያ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይጠየቃል።

(f) በማንኛውም ጊዜ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት ከመንግስትም ሆነ የግል የመድን ዋስትና ክፍያ ለመጠየቅ ከወላጆች ፈቃድ በሚጠየቅበት ጊዜ ወላጆች የክፍያ ሥርዓት እና የክፍያዎች ፖሊሲ እንዲደርሳቸው ይደረጋል።

(g) በ 34 CFR §303.521(a)(4)(iv) መሰረት የመንግስት የመድን ዋስትና ወይም ጥቅማ ጥቅም ያላቸው ቤተሰቦች የግል የመድን ዋስትና ወይም ጥቅማጥቅም ካላቸው ቤተሶች በላይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ክፍያ እንዲከፍሉ አይደረጉም።

(h) በ 34 CFR §303.520(b)(1) መሰረት፣ ቤተሰቦች አፐል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ እና የግል የመድን ዋስትና ያላቸው ከሆነ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪዎች የሚከተሉትን ለማድረግ የወላጅ ፈቃ ይጠይቃሉ፡-

(1) በ IFSP ላይ ለተካተቱት የመጀመሪያ ጊዜ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ክፍያ ለመፈጸም የቤተሰቡን የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን ለመጠቀም፤

(2) በ IFSP ላይ ለተካተቱት የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ክፍያ ማንኛውም የድግግሞሽ፣ ርዝመት፣ የቆይታ ጊዜ ወይም የአገልግሎቶች የጥንካሬ መጠን ጭማሪ ክፍያ ለመፈጸም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን ለመጠቀም፤

(i) የ ESIT አገልግሎት ሰጪ የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ክፍያውን ከአፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ እና የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትናን እና ተቀናሾችን ጨምሮ ክፍያ የመጠየቅ ኃላፊነት አለበት።

(j) የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግበት የሚገባ የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ክፍያ በግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና ክፍያ እንዲፈጸም ሲፈለግ ፈቃድ ለማግኘት አስፈላጊው ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት። ይግባኝ በሚቀርብበት ጊዜ፣ በቤተሰቡ ጥያቄ መሰረት FRC ወይም ሌላ አግባብ የሆነ ሠራተኛ ዕገዛ ሊያደርግ ይችላል። ቤተሰቡ፣ መክፈል አለመቻል የሚለውን ትርጓሜ ያሟላል ካልተባለ በስተቀር በልጁ በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ውስጥ ለተካተቱት የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና የአሹራ፣ የትብብር ክፍያዎች፣ የጋራ የመድን ዋስትና እና ተቀናሾች ክፍያ ኃላፊነት አለበት።

(k) ወላጅ ወይም ቤተሰብ ለጨቅላ ሕጻን ልጃቸው ወይም ድክ ድክ ለሚሉ ሕጻናት አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን ወይም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን ለማገናኘት ፈቃድ ካልሰጡ፣ የፈቃድ አለመሰጠት የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ እንዲደረግባቸው የሚፈለጉ ማናቸውንም የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለማዘግየት ወይም ለመከልከል እንደ ምክንያት አይወሰዱም። ነገር ግን፣ የፈቃድ አለመኖር በወርኃዊ የክፍያ ሠንጠረዥ ላይ እንዲመደቡ ያደርጋል (የክፍያ ሥርዓት እና የክፍያዎች ፖሊሲን 28.ለ.9 ይመልከቱ)

(l) የዋሽንግተን የመድን ዋስትና ኮሚሽን ቢሮ የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን አስመልክቶ ጥያቄ ያላቸውን ወላጆች ለማገዝ ዝግጁ ነው። ከክፍያ ነጻ ሆትላይን 1-800- 562-6900 ነው።

### 14.C.4. ለቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ አጠቃላይ መመሪያዎች

(a) የ ESIT የመጀመሪያ ደረጃ ብቁነት ከተረጋገጠ በኋላ፣ ሁሉም ቤተሰቦች የገቢ እና ወጪ መረጃ እንዲያቀርቡ፣ ማንነትን ለመግለጽ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃድ እንዲሰጡ እና የመንግስት እና/ወይም የግል የመድን ዋስትና ሽፋንን ለማገናኘት ፈቃድ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። የገቢ እና ወጪ መረጃ የሚፈለገው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ለመፍታት ነው።

  (1) የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ አገልግሎቶች አንድ ቤተሰብ አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን ለማገናኘት ፈቃድ ካልሰጠ፤

  (2) አንድ ቤተሰብ ለአፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ለማመልከት ካልተስማማ፤

  (3) የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ አገልግሎቶች አንድ ቤተሰብ የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን ለማገናኘት ፈቃድ ካልሰጠ፤

  (4) የግል የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትናን፣ እና ተቀናሾን የመክፈል ችሎታ እና መክፈል አለመቻልን መወሰን፤ እና፣

  (5) አንድ ቤተሰብ የመንግስትም ሆነ የግል የመድን ዋስትና ሽፋን ከሌለው እና ክፍያ የሚወሰን ከሆነ።

(b) የቀረበው የገቢ እና ወጪ መረጃ የቤተሰቡ አጠቃላይ የተስተካከለ ዓመታዊ ገቢ ከፌዴራል የድህነት ወለል (FPL) 200% ወይም ከዚያ በላይ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ፣ ቤተሰቡ የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን ከመጠቀም ጋር የተያያዙ የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ወይም ተቀናሾችን እንዲከፍሉ ወይም ተፈጻሚ ከሆነ በአፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ሽፋን በኩል እንዲከፍሉ ይደረጋል።

(c) የቀረበው የገቢ እና ወጪ መረጃ የቤተሰቡ አጠቃላይ የተስተካከለ ዓመታዊ ገቢ ከፌዴራል የድህነት ወለል (FPL) ከ200% በታች መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ፣ በቤተሰብ መጠን መሰረት ቤተሰቡ ማንኛውንም ዓይነት የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን ከመጠቀም ጋር የተያያዙ የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ወይም ተቀናሾችን እንዲከፍሉ ወይም ተፈጻሚ ከሆነ በአፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ሽፋን በኩል እንዲከፍሉ አይደረግም።

(d) የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ወይም ተቀናሾችን እንዲከፍሉ ለተደረጉ ቤተሰቦች በሙሉ የክፍል ሐ የመጨረሻ አማራጭ ክፍያዎቻችንን ጨምሮ የሌሎች ኤጀንሲዎችን የገንዘብ ድጋፍ እነዚህን ወጪዎች ለመሸፈን ጥቅም ላይ ይውላል።

### 14.C.5. መክፈል አለመቻል

(a) ቤተሰቦች የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትናን ወይም ተቀናሾችን “መክፈል አለመቻል”ን በማንኛውም ጊዜ ከቤተሰብ መረጃ አስተባባሪያቸው (FRC) ወይም ከሌሎች አግባብ የሆኑ ሠራተኞች መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄውን ከተቀበለ በኋላ FRC ቤተሰቡ የገቢ እና ወጪ ማረጋገጫ ቅጽ እንዲሞላ ያግዛል።

(b) “መክፈል አለመቻል” የሚወሰነው በገቢ እና ወጪ ማረጋገጫ ቅጽ ውጤቶች ሲሆን እነዚህም የቤተሰቡ ተመላሽ የማይደረግ አመታዊ የሚፈቀድ ወጪ ከቤተሰቡ አመታዊ የተስተካከለ ገቢ ከ10 በመቶ በላይ መሆኑን ማሳየት አለበት።

  (1) “መክፈል አለመቻል” ውሳኔ ከተሰጠ፣ የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትና ወይም ተቀናሾችን ለመክፈል የክፍል ሐ የመጨረሻ አማራጭ ክፍያዎች ወይም የሌሎች ኤጀንሲዎች የገንዘብ ድጋፍ ጥቅም ላይ ይውላል።

  (2) አገልግሎቶቹ ይበልጥ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊቀርቡ የሚችሉ ከሆነ፣ ክፍል ሐ ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪን መጠቀም ወይም ከግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና ጋር ተመሳሳይ የሆነ ወጪ እንዲከፍል አይገደድም።

(c) የቤተሰብ “መክፈል አለመቻል” አቋም ቢያንስ በየአመቱ እና ቤተሰብ ሲጠይቅ ደግሞ ከዚያ ባነሰ ጊዜ ይገመገማል እንዲሁም ይሻሻላል።

(d) በ IFSP ትግበራ ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ የቤተሰቡ “መክፈል አለመቻል” ሁኔታ ከተለወጠ በተቻለ ፍጥነት ለ FRC ማሳወቅ እና መክፈል አለመቻል በድጋሚ እንዲታይ መጠየቅ አለባቸው። በጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና ላይ ለውጦች በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ ለውጦቹን ከ FRCያቸው ጋር መነጋገር አለባቸው።

(e) በ34 CFR §303.521(a)(4)(ii) መሰረት፣ አንድ ቤተሰብ “መክፈል አለመቻል” የሚለውን ትርጓሜ ካሟላ ሁሉም በልጁ IFSP ላይ የተዘረዘሩ አገልግሎቶች ቤተሰቡ ምንም አይነት ወጪ ሳያወጣ ይሰጣሉ። በተጨማሪም የቤተሰቡ መክፈል አለመቻል የክፍል ሐ አገልግሎቶች እንዲዘገዩ ወይም እንዲከለከሉ አያደርግም።

(f) የቤተሰቡ የመክፈል አቅም ካልተረጋገጠ፣ ቤተሰቡ የግል ጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትናን እና ተቀናሾችን የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል።

### 14.C.6. ክፍያዎች

(a) የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ አገልግሎቶች አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ወይም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትናን (በመጀመሪያ እና አገልግሎቶች ሲጨመሩ) ለማገናኘት ፈቃዳቸውን የሰጡ ቤተሰቦች ክፍያዎችን ከመፈጸም ይታለፋሉ።

(b) አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ሽፋን ያላቸው፣ መክፈል አለመቻል የሚለውን ትርጓሜ የሚያሟሉ እና አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ሽፋናቸውን የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ የክፍል ሐ አገልግሎቶች መጠቀምን የከለከሉ ቤተሰቦች ክፍያዎችን ከመፈጸም ይታለፋሉ።

(c) ከሚከተሉት አንዱ በሚያጋጥምበት ጊዜ ወርኃዊ የክፍያ ሠንጠረዥ ላይ የሚደረግ ምደባን ለመወሰን የቤተሰብ የገቢ እና ወጪ መረጃ ጥቅም ላይ ይውላል:-

  (1) አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድ ወይም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና የሌላቸው ቤተሰቦች በቤተሰብ መጠን እና በተስተካከለ ዓመታዊ ገቢ መሰረት በወርኃዊ የክፍያ ሠንጠረዥ ላይ ይመደባሉ።

  (2) የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ የክፍል ሐ አገልግሎቶች የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋናቸውን/የመድን ዋስትናቸውን ለመጠቀም ፈቃድ የከለከሉ እና የገቢ እና የወጪ መረጃን የሰጡ ወላጆች በቤተሰብ መጠን እና በተስተካከለ ዓመታዊ ገቢ መሰረት በ ወርኃዊ ክፍያ ሠንጠረዥ ላይ ይመደባሉ።

(d) የገቢ እና የወጪ መረጃን ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑ ወላጆች በቤተሰብ መጠን መሰረት በከፍተኛ መጠን ወርኃዊ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋሉ።

### 14.C.7. ያልተከፈሉ ክፍያዎች

(a) በገቢ እና ወጪ ማረጋገጫ ቅጽ መረጃ መሰረት አንድ ቤተሰብ የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው ለሚገቡ አገልግሎቶች የትብብር ክፍያዎችን፣ የጋራ የመድን ዋስትናን፣ ተቀናሾችን ወይም ክፍያዎችን መክፍል እያለበት ሳይከፍል ከቀረ፣ እነዚህ አገልግሎቶች ይከለከላሉ። ይህም የሚከሰተው የ90 ቀን የሚሆኑ ኢንቮይሶች ክፍያዎች ሳይከፈሉ ሲቀር ነው።

(b) ቤተሰብ፣ አገልግሎት ሰጪዎች እና FRC ከ FRC አገልግሎቶች፣ ግምገማ እና የ IFSP ዝግጅት እና ግምገማ፣ የሥነ-

ስርዓት ጥበቃዎች ውጪ ሌሎች አገልግሎቶች በቤተሰቡ እና በአጊ.ጋዩ ኤጀንሲ አማካኝነት የክፍያ ዕቅድ ካልወጣ በስተቀር እንደማይቀጥሉ የሚገጽ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

(c) በቤተሰቡ እና በአገሊ.ጋዩ ኤጀንሲ የክፍያ ዕቅድ ከወጣ በኋላ የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግላቸው የሚገቡ አገልግሎቶች ክፍያ መቀጠል እንደሚችል ለቤተሰብ፣ ለ FRC እና ለአገልግሎት ሰጪዎች ማሳወቂያ ይላካል።

### 14.C.8. ትርጓሜዎች

ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል፣ የሚከተሉት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡-

(a) "<u>የሚፈቀዱ ወጪዎች</u>" ማለት፡-

(1) ለልጅ ማሳደጊያ/ቀለብ በቤተሰቡ ለሶስተኛ ወገን የሚከፈል፤

(2) ወላጅ ስራ ሲሰራ ወይም ትምህርት ሲማር ለልጅ ተንከባካቢ በቤተሰቡ የሚፈከል ወጪ፤ እና

(3) በቤተሰቡ የሚከፈሉ ተመላሽ የማይደረጉ የሕክምና፣ የታዘዙ መድሃኒቶች፣ እና የጥርስ ሕክምና ወጪዎች፣ የአሹራ ክፍያን፣ የትብብር ክፍያዎችን እና ተቀናሾችን ጨምሮ።

(b) "<u>የጋራ የመድን ዋስትና</u>" ማለት፡- ለጤና እንክብካቤ ሽፋን በወላጅ(ጆች) የወጪ መጋራት የሚከፈል ነው። ለምሳሌ፣ ለአገልግሎት ወጪዎች የጤና እንክብካቤ ሽፋኑ 80% ሲከፈል ወላጅ(ጆች) ደግሞ 20% ይከፍላሉ።

(c) "<u>የትብብር ክፍያ</u>" ማለት፡- አንድ ወላጅ ለአንድ የተወሰነ አገልግሎት፣ መሳሪያ ወይም አቅርቦቶች በጤና እንክብካቤ የመድን ዋስትና ፖሊሲ አማካኝት ለጤና አገልግሎት ሰጪያቸው የሚከፍሉት ክፍያ ነው። ክፍያ የሚፈጸመው ለአገልግሎት ወይም ለአቅርቦት አቅራቢው በቀጥታ ነው።

(d) "<u>ተቀናሽ</u>" ማለት ሽፋን ላላቸው የሕክምና/የጥርስ ሕክምና ወጪዎች ወላጅ(ጆች) ወጪ የሚያወጣባቸው እና ጥቅማ ጥቅሞቹ ከመሰጠታቸው በፊት የሚከፍላቸው ናቸው። የትብብር ክፍያ እና/ወይም የጋራ የመድን ዋስትና በተቀናሾች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

(e) "<u>የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ ሊደረግባቸው የሚገቡ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች</u>" ማለት የእያንዳንዱን ብቁ የሆነ ልጅ የዕድገት ፍላጎቶች ለማሟላት በ IDEA የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ክፍል ተፈላጊ የሆኑ እና የልጁን ዕድገት ከማፋጠን ጋር በተያያዘ ለቤተሰቡ የሚያስፈልጉ አጋዥ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች፣ የጤና አገልግሎቶች፣ የማስታመም አገልግሎቶች፣ የሥነ-ምግብ አገልግሎቶች፣ ማማከር፣ ኦኪዩፔሽናል ቴራፒ፣ አካላዊ ሕክምና፣ የሥነ-ልቦና አገልግሎቶች፣ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ አገልግሎቶች፣ እና የንግግር-ቋንቋ አገልግሎቶች ናቸው። አገልግሎቶቹ የሚመረጡ ከወላጆች ጋር በመተባበር ነው። በመንግስት ቁጥጥር ብቁ በሆኑ ባለሙያዎች በዋሽንግተን ግዛት የ"ብቁነት" ትርጓሜ እና በግል በሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) መሰረት ይሰጣሉ።

(f) "<u>የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ኮንትራክተር (የአካባቢ መሪ ኤጀንሲ)</u>" ማለት የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት ከጨቅላነት ጊዜ ትምህርት ክፍል (DEL) የጨቅላ ሕጻናት እና ድክ ድክ የሚሉ ሕጻናት የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት (ESIT) ጋር ውል የገባ እና አገልግሎቶች በጸደቀው የዋሽንግተን ግዛት የድጋፍ ማመልከቻ መሰረት መስጠታቸውን የሚያረጋግጥ በአካባቢው የተወከለ ኤጀንሲ ወይም ድርጅት ነው።

(g) "<u>የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት ሰጪ</u>" ማለት የ IDEA፣ የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን የሚሰጥ የአካባቢው የመንግስት ወይም የግል አገልግሎት ሰጪ ወይም ኤጀንሲ ነው።

(h) "<u>የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ</u>" ማለት ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ለሚሰጡ አገልግሎቶች (1) የቤተሰቡን የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና፣ እና/ወይም (2) አፕል የልጆች ጤና/ሜዲኬይድን በማገናኘት ወይም (3) የቤተሰብ የወጪ ተሳትፎ እንዲደረግባቸው ለሚፈለግ የ IDEA የክፍል ሐ የጨቅላነት ጊዜ አገልግሎቶች ክፍያ በመፈጸም የሚያደርጓቸው የገንዘብ አስተዋጽኦዎች ናቸው።

(i) "<u>የቤተሰብ መረጃ አስተባባሪ (FRC)</u>" ማለት ብቁ የሆነን ልጅ እና ቤተሰቡ በግል በሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) መሰረት ተለይተው የተቀመጡ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን እና ሌሎች መረጃና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ እና የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን መብቶች እና የሥነ-ስርዓት ጥበቃዎችን በማግኘት ዙሪያ የሚያግዝ ግለሰብ ነው።

(j) "<u>ከፍተኛ ተቀናሽ/የአደጋ ጊዜ እንክብካቤ ዋና የሕክምና ሽፋን</u>" ማለት በዓመታዊ የ 5,000 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ ተቀናሽ የሚደረግበት የመድን ዋስትና ሲሆን ለጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎት የክፍያ ዓላማዎች ከእሳቤ ውስጥ አይገባም።

(k) "<u>በግል የሚሰጥ የቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP)</u>" ማለት በ IDEA የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ክፍል መሰረት ለአንድ ልጅ እና ለቤተሰቡ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን ለመስጠት በጽሁፍ የሚዘጋጅ ዕቅድ ነው።

ዕቅዱ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

(1) በቤተሰብ እና አግባብ በጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ላይ ተሳታፊ በሆነ ሠራተኛ በጋራ መዘጋጀት፤

(2) በልጁ ላይ በዘርፈ ብዙ ባለሙያዎች በሚደረግ ግምገማ እና ምዘና ላይ የተመሰረተ፤

(3) በወላጅ ፈቃድ፣ የወላችን ሐብት፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች እና ከልጁ ዕድገት ጋር በተያያዘ የሚያሳስቧቸውን ነገሮች ማካተት አለበት፤ እንዲሁም

(4) የልጁን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት እንዲችል የቤተሰቡን አቅም ለማሳደግ አስፈላጊ የሆኑ ልዩ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን መግለጫ ማካተት አለበት።

(l) " የ<u>IFSP የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች</u>" ማለት በአንድ ጨቅላ ወይም ድክ ድክ የሚል ሕጻን IFSP ላይ የተገለጹ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች።

(m) "<u>ወላጅ</u>" ማለት፡-

(1) የልጁ ተፈጥሮ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ፡-

(2) በግዛት ሕግ፣ ደንቦች ወይም የውል ግዴታዎች መሰረት በግዛት ወይም በአካባቢ ሕግ አሳዳጊ ወላጅ እንደ ወላጅ ሆኖ ማገልገል ካልተከለከለ በስተቀር፣ አሳዳጊ ወላጅ፡-

(3) የልጁ ወላጅ ሆኖ እንዲያገለግል አጠቃላይ ፈቃድ የተሰጠው አሳዳጊ ወላጅ፣ ወይም ለልጁ የጨቅላነት ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶችን፣ የትምህርት፣ የጤና ወይም የዕድገት ውሳኔዎች እንዲወስን ፈቃድ የተሰጠው (ነገር ግን ልጁ በግዛቱ ዋርድ ስር የሚገኝ ከሆነ ግዛቱን አይጨምርም)፤

(4) በተፈጥሮ ወይም በጉዲፈቻ ወላጅ ምትክ የሚገለግል (አያቶችን፣ የአንጀራ አያቶችን ወይም ሌሎች ዘመዶችን ጨምሮ) ከልጁ ጋር የሚኖር፣ ወይም ለልጁ ደህንነት ሕጋዊ ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ፤ ወይም

(5) ምትክ ወላጅ በሕጉ 34 CFR
§303.422 ወይም 639(a)(5) መሰረት የተሾመ።

(n) "<u>የመንግስት ወይም የግል የጤና እንክብካቤ ሽፋን/የመድን ዋስትና</u>" ማለት፡-

(1) "የግል የመድን ዋስትና" – ለልጁ እና/ወይም ለቤተሰቡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ በሶስተኛ ወገን ሲሸፈን። ይህም ከስራ ቅጥር ጋር የተያያዙ እና በግል የተገዙ የመድን ዋስትናዎችን፣ የሕክምና ቁጠባ ሂሳቦችን እና የጤና ቁጠባ ሂሳቦችን ያካትታል።

(2) "ትራይኬር/ትራይዌስት" – ለጦር ሰራዊት ሰዎች እና ለቤተሰቦቻቸው የሚሆን የጤና ጥቅማጥቅም ፕሮግራም።

(3) "የመንግስት የመድን ዋስትና" – በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት (በግዛት እና/ወይም በፌዴራል) ለልጆ የጤና እንክብካቤ አገልግቶች የሚደረግ ክፍያ። ይህን የአፐል የልጆች ጤና ፕሮግሞች የሆኑትን ቤዚክ ሄልዝ ፐላስ፣ ሜዲኬይድ፣ ሜዲኬይድ ሄልዚ ኦፐሽንስ እና
የሕጻናት ጤና መድን ፕሮግራም ያካትታል።

(o) "<u>የግዛት መሪ ኤጀንሲ (SLA)</u>" ማለት የጨቅላነት ጊዜ ትምህርት ክፍል ነው።

(p) "<u>ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ</u>" ማለት፡-

(1) ከቅጥር እና/ወይም ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ በሚከተሉት ብቻ ባይወሰንም የሚከተሉተን የሚያካትት ዓመታዊ ገቢ፡- የመንግስት ድጋፍ ስጦታ፣ የስራ አጥነት ካሳ፣ የአካል ጉዳት፣ የተቀበለ ልጅ ድጋፍ/የቀለብ ክፍያ፣ ሌሎች ገቢዎች ከሚከተሉት በአንዱ የሚፈቀድ፡-

(i) የቅርብ ጊዜ የፌዴራል ገቢ ታክስ ተመላሽ *(ቅጽ 1040=መስመር 22፤ 1040A=መስመር 15፤ 1040EZ=መስመር)*;

(ii) የቅርብ ጊዜ W2(ዎች) እና/ወይም 1099(ዎች) *(ቅጽ W2=መስመር 1፤ 1099=የመስመሮች 1፣ 2 & 3 ጠቅላላ ውጤት)*፤

(iii) ያለፉት ሁለት (2) ተከታታይ የደሞዝ መክፈያ ቁራጮች፤ ወይም

(iv) የደሞዝ ወይም የቀን ክፍያ የጽሁፍ መግለጫ (የኩባንያ/ቀጣሪውን ስም፣ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር እና ተቆጣጣሪ/የሰው ሀብት ሠራተኛ ፊርማ)

(2) የደንብ ልብስ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ አባላት በፈቃድ እና የገቢ መግለጫ ላይ የሚገኙትን የሚከተሉን ጠቅላላ ክፍያዎች ያካቱ፡-

(i) መሰረታዊ ክፍያ (ስራ ሰርተው የሚያገኙት ገቢ)፤ እና

(ii) ተቆራጮች (ስራ ሳይሰሩ የሚያገኙት ገቢ)

(iii) ተቆራጩ የተከፈለው እና ተቀናሽ የተደረገው በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ ከሆነ የአደገኝ እሳት ክፍያን፣ የቅርብ ጊዜ አደጋን ክፍያ ወይም ነጻ ወይም መሰረታዊ የቤት ተቆራጭን አያካቱ።